የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን

# የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት /2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የተመደበለትን በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኮሚሽኑ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን  የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኮሚሽኑ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኮሚሽኑ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኮሚሽኑ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት
- የሂሣብ ማመዛዘኛ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት

የኮሚሽኑን የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀትና በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪ እና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደርን አዋጅ ደንብና መመሪያ የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**የወጪ ሂሳብ፤**

1. ተቀናሽ ያልተደረገ የህክምና መዋጮ ብር 18,482.52 ተገኝቷል፡፡
2. ከውሎ አበል መመሪያ ውጭ ብር 2,644.00 የውሎ አበል በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
3. የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት የውሎ አበል እና የመጓጓዣ ወጪ በድምሩ ብር 547,447.30 ተገኝቷል፡፡

**የተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

4. በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 183,887.56 ተገኝቷል፡፡
5. ለሚመለከተው አካል ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 166,795.14 ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 ከተገለጹት በስተቀር በእኛ አስተያየት የኮሚሽኑ የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች**

6. በሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ብር 5,021,197.72 (31.93%) ተገኝቷል፡፡
7. **ንብረት፤**

- በርከት ያሉ የተለያዩ የመኪና መለዋወጫዎች (Spare Parts and Accessories) አገልግሎት የሚሰጡ ቢሆንም መ/ቤቱ የማይጠቀምባቸው ለዓመታት ከአላቂ የንብረት መጋዘን ውስጥ ሳይወገዱ ተከማችተው የተገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ፕሪንተሮች ፤ዲስክ ቶፕና ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች የመኪና ጎማዎች ወንበሮች፤ ፍላሽ ዲስኮች እና የመሳሰሉት በርከት ያሉ አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች በንብረት መጋዘን ውስጥ ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

- ኮድ 4-03224 ቲዮታ ላንድ ክሮዘር ፤ኮድ 4-09989 ቮልቮ አውቶሞቢል፤ 2 ሞተር ሳይክል ኢ.ት-1363 እና ኢ.ት- 1206 ከ 5 አመት በላይ በብልሽት የቆሙ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ኮድ ኢ.ት-09989 ከ18/11/97 ዓ.ም ጀምሮ መ/ቤቱ የሚጠቀምበት ነገር ግን በመ/ቤቱ ስም ያልተዛወረ መሆኑ እና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌለው መሆኑ፤ 3 ተሽከርካሪዎች ኮድ 4-03202 ፤4-13969፤4-08715 መ/ቤቱ የሚጠቀምበት ነገር ግን የንብረት ባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩ (ሊብሬው) የሌላ መስሪያ ቤት የሆነ በኮሚሽኑ ስም አለመዛወሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከሠላምታ ጋር

------------------------

አንድነት ብዙሰው

የኦዲት ሥራ አስኪያጅ

ቀን ፡10/06/2012